# አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉለሌ ክፍለ ከተማ የ2018 ዓ.ም 6ኛ ክፍል የ1ኛ መንፈቅ አመት የግብረ ገብ ት/ት ሞዴል ፈተና



LIVEWORKSHEETS

## I. <u>ለሚከተሉት ጥያቄዎች በማንበብ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በመልስ መስጫ ወረቀት ላይ አጥቁሩ</u>

1. ከሚከተሉት ስለሃላፊነት ለማወቅና ለመማር ከምንችልባቸው መንገዶች አንዱ ነው::

ሀ/ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ጥንቃቄ አለማድረግ ለ/ ለቤተሰብ አገልግሎት መስጠት

ሐ/ ጓደኛና ጎረቤትን አለማገዝ መ/ ስራን በአግባቡ አለመስራት

2. ኃላፊነት ማለት ምን ማለት ነው?

ሀ/ ለድርጊቶች ተጠያቂነትን መውሰድ ለ/ የተሰጠን የስራ ድርሻ አለመወጣት

ሐ/ ኃላፊነትን ለመቀበል ዝግጁ አለመሆን መ/ ታማኝ አለመሆን

3. ከሚከተሉት የኃላፊነትን አይነቶች የሆነው የቱ ነው?

ሀ/ በትህትና መናገር ለ. እርስ በርስ መከባበር

ሐ. ሐገራዊ ኃላፊነት መ. በጓደኛ አለመቅናት

4. ከሚከተሉት አማራጮች ከተማሪ የሚጠበቅ ግብረገባዊ የኃላፊነት አይነት የሆነው የቱ ነው?

ሀ/ ቃልን መጠበቅ ለ/ሌሎችን መርዳት

ሐ/ ሀ እና ለ መልስ ናቸው መ/ ግብር መክፈል

5. ከሚከተሉት አማራጮች ቃልን መጠበቅ ስህተት የሆነው የቱ ነው?

ሀ/ አንድ ሰው የተናገረውን የማይፈጽምበት ነው

ለ/ አንድን ነገር እንደሚሰራው የሚያረጋግጥበት ነው

ሐ/ አንድን ነገር እንደሚያደርገው የሚያረጋግጥበት መግለጫ ነው

መ/ ኃላፊነቱን መወጣት ማለት ነው

6. ከሚከተሉት ተማሪዎች በትርፍ ጊዜያቸው መሳተፍ የሌለባቸው ማህበረሰባዊ ተሳትፎ ነው

ሀ/ በትምህርት ዘመቻ ላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ

ለ/ ገንዘብ በማሰባሰብ በጎ አድራጎት ስራ ላይ መሳተፍ

ሐ/ የተሰጣቸው ኃላፊነት መወጣት

መ/ በተለያዩ ክበባት አለመሳተፍ

7. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ጠንካራ የስራ ባህል መገለጫ አይደለም::

ሀ/ ውጤታማ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል ለ/ በፍጥነት እንዲያድጉ ያደርጋል

ሐ/ ጤናማ እንዲሆኑ አያደርግም መ/ ታታሪ እንዲሆ አያደርግም

8. ከሚከተሉት አንዱ ጠንካራ የስራ ባህል አስፈላጊነትን ይገልፃል::

ሀ/ ከኋላቀርነት አለመላቀቅ ለ/ ድህነትን ለማጥፋት

ሐ/ በፍጥነት ለማድረግ መ/ ለ እ ሐ መልስ ናቸው



LIVEWORKSHEETS

9. ከሚከተሉት አንዱ ታታሪ የሆኑ ተማሪዎች መገለጫ የሆነው የቱ ነው?

ሀ/ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ በክበባት አለመሳተፍ

ለ/ በድንገት ያመለጧቸው ማስታወሻዎች ከሌሎች ተማሪዎች ይወስዳሉ

ሐ/ በመደበኛነት ትምህርታቸውን አይከታተሉም

መ/ የቤት ስራቸውን በሰዓቱ አያጠናቅቁም

10. ልጆችን ስራ ማለማመድ ለምን ይጠቅማል?

ሀ/ እንዴት መስራት እንዳለባቸው እንዲያውቁ ለ/ ጥሩ የስራ ባህልን እንደያዳብሩ

ሐ/ ጠንካራ የስራ ባህልንና እሴትን ይዘው እንዲያድጉ መ/ የልጆች ጉልበት ብዝበዛ ስለሆነ

11. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የንባብ ልምድን ለማዳበር የሚያግዝ ነው ።

ሀ/ በየቀኑ ለማንበብ ጊዜ አለመስጠት ለ/ ደስ የሚለንን መጽሐፍ ብቻ አለማንበብ

ሐ/ በሁሉም ቦታ መጽሐፍትን ይዞ መንቀሳቀስ መ/ ለማንበብ ዝግጁ አለመሆን

12. የተወሰነ መረጃ ብቻ ለመፈለግ ሲባል በፍጥነት ለማንበብ የምንጠቀምበት ስልት ነው፡፡

ሀ/ የሀረግ ንባብ ለ/ የአሰሳ ንባብ

ሐ/ አላማ ያለው ንባብ መ/ የዳሰሳ ንባብ

13. ከሚከተሉት ንባብን ለመማር ከምንጠቀምባቸው ስልቶች መካከል አንዱ ነው፡፡

ሀ/ ዓላማ ያለው ንባብ ለ/ ደስ የሚለንን መጽሐፍ ማንበብ

ሐ/ ለማንበብ ጊዜ መመደብ መ/ የመጽሐፍ ክበብ አባል መሆን

14. ከሚከተሉት አንዱ አጠቃላይ ሀሳብን ለማግኘት ሲባል የምንጠቀመው የንባብ አይነት የትኛው ነው፡፡

ሀ/ የመረጃ ቃላት ለ/ የሀረግ ንባብ ሐ/ መቃኘት መ/ የአሰሳ ንባብ

15. አንድ ሰው ከሚያጋጥመው በርካታ አማራጮች ውስጥ ሁሉንም በመገምገም አማራጭ የመውሰድና መደምደሚያ ላይ የመድረስ ሂደት ነው፡፡

ሀ/ አሳቢነት ለ/ ምክንያታዊነት ሐ/ ውሳኔ መ/ ችግር መለየት

16. ከሚከተሉት የግብረገባዊ ውሳኔ ችሎታ ባህሪያት የሆነው የቱ ነው፡፡

ሀ/ አሳቢነት ለ/ የውሳኔ አሰጣጥ ሐ/ ግብረገባዊ ውሳኔ መ/ መፍትሄ መስጠት

17. ከሚከተሉት አንዱ ጥንቃቄ የተሞላበት እና ስልታዊ እርምጃዎችን ያካትታል፡፡

ሀ/ ምክንያታዊነት ለ/ ምክንያታዊ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት

ሐ/ ችግር መለየት መ/ አሳቢነት

18. ከሚከተሉት አማራጮች የግብረገባዊ ውሳኔ አሰጣጥ ቅደም ተከተል ውስጥ አይካተትም፡፡

ሀ/ ምክንያታዊ ውሳኔ ለ/ ችግሩን መለየት ሐ/ መወሰን መ/ መገምገም



LIVEWORKSHEETS

19. ከሚከተሉት አንዱ ግብረገባዊ ውሳኔ መስጠት አስፈላጊነት አይደለም፡፡

ሀ/ ለወደፊት ጥሩ ውሳኔዎችን ለመወሰን ለ/ የተሻለ ምርጫ ለመወሰን

ሐ/ የበዛ ቁርጠኝነት አለመኖር መ/ ጥሩ ውሳኔ ለመወሰን

20. ባለው ችግር ላይ በመመስረት ትክክለኛውን ምርጫ የመምረጥ ችሎታ የውሳኔ አሰጣጥ ጉዳይ ነው፡፡

ሀ/ በማህበረሰቡ የሚሰጥ ግምት ለ/ የግብረገባዊ ውሳኔ

ሐ/ የውሳኔውን ውጤት መገምገም መ/ መወሰንና መከታተል

21. በግብረገባዊ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶች ስንት ናቸው ?

ሀ/ ስምንት ለ/ አስር ሐ/ ሰባት መ/ 9

22. አንድ ሰው ስለ ነገሮች ባለው መሰረታዊ ግላዊ እምነት ኢ-ተለዋዋጭ አቋምን የማሳየት ብቃት ነው፡፡

ሀ/ ሃቀኝነት ለ/ ራስን በሌሎች ቦታ አድርጎ ማየት ሐ/ ድፍረት መ/ምሉዕነት

23. ከ ሚ ከ ተ ሉ ት ግብረገባዊ ምሉዕነት ያለው ሰው የሚፈጽማቸው ድርጊቶች አንዱ አይደለም፡፡

ሀ/ ሀቀኝነት ለ/ መወሰን ሐ/ ድፍረት መ/ ስለሌሎች ማሰብ

24. አንድ ሰው ትክክል ነው ብሎ የሚያምንበትን ነገር እንዲተገብር የሚያደርግ ውስጣዊ ችሎታ ነው፡፡

ሀ/ ስለሌሎች ማሰብ ለ/ ሃቀኝነት ሐ/ ራስን በሌሎች ቦታ አድርጎ ማየት መ/ድፍረት

25. ከሚከተሉት አንዱ የግብረገብ ምሉዕነት ጠቀሜታ አይደለም፡፡

ሀ/ ጠንካራ የሆነ ሰራተኛ መሆን ለ/ ማህበራዊ ትስስር አለማጠንከር

ሐ/ ከሌሎች የምንፈልገው ክብር መ/ ችግር የመፍታት ብቃት

26. ከሚከተሉት አንዱ የግብረገብ ምሉዕነት የተላበሰ ሰው ባህሪያት ነው፡፡

ሀ/ የህይወት መመሪያዎችን መከተል ለ/ የማይፈልጉትን ለማድረግ ቃል መግባት

ሐ/ የሚናገሩትን ሆነው አለመገኘት መ/ የሕይወት መርሆችን አለመከተል

27. አንድ ሰው የሚፈጽመው ድርጊት እውነተኛ ማንነቱን የማያሳይ ከሆነ …… ይባላል፡፡

ሀ/ ሀቀኛ ለ/ ታማኝ ሐ/ አስመሳይ/ግብዝ መ/ ምሉዕነት

28. ዜጎች የሃገሪቱን ህግ ለማክበር ያላቸው ዝግጁነት/ ቁርጠኝነት …… ይባላል፡፡

ሀ/ የህግ ተገዥነት አስፈላጊነት ለ/ ለህግ ተገዥነት

ሐ/ ፍቃደኝነት መ/ የህግ ተገዥነት እሴት

29. ከሚከተሉት አንዱ ከየህግ ተገዥነትና ዜጎች ሙሉ ነፃነታቸውን እንዲያገኙ ይረዳል፡፡

ሀ/ ሙሉ ነፃነት ማግኘት ለ/ የዜጎች ፍላጎት መጠበቅ

ሐ/ ሰላምን መጠበቅ መ/ ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል



LIVEWORKSHEETS

30. ከሚከተሉት አንዱ የህዝቦች ይሁንታ መገለጫ ነው፡፡

ሀ/ ሰላምን መጠበቅ ለ/ የዜጎች ፍላጎት መጠበቅ

ሐ/ ሙሉ ነፃነት ማግኘት መ/ ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል

31. ሠዎች እንደፈለጉ መርጠው የሚያከብሯቸውና የሚተዋቸው አይደሉም፡፡

ሀ/ ህጎች ለ/ ሰላምን መጠበቅ ሐ/ ኃላፊነት መ/ የህግ የበላይነት

32. የሀገሪቱን ህግ የማወቅና የማክበር የሁሉም .......... ግዴታ ነው፡፡

ሀ/ ግለሰብ ለ/ ማህበረሰብ ሐ/ አባል መ. ተማሪ

33. ከሚከተሉት አማራጮች አንዱ ለህግ ተገዥ አለመሆን የሚያስከትለው አሉታዊ ውጤት ነው፡፡

ሀ/ የሰላም መኖር ለ/ ሙስና

ሐ/ ሰብአዊ መብት አለመጣስ መ/ ወገንተኝነት አለመኖር

34. ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ለባለስልጣናት ገንዘብ መስጠት ማለት ነው፡፡

ሀ/ ሙስና ለ/ የዝምድና ወገንተኝነት ሐ/ ማጭበርበር መ/ ጉቦ መስጠት

35. ከሚከተሉት የመልካም ባህሪ ምሳሌዎች ውስጥ አይካተትም፡፡

ሀ/ ትሁት መሆን ለ/ በራስ አለመተማመን

ሐ/ ፈቃድን መጠየቅ መ/ አመስጋኞች መሆን

36. ታማኝነትን ሀቀኝነትን መተግበርና ውሸት መናገርን አጭበርባሪነትን ማስወገድ መቻል ነው፡፡

ሀ/ ሀቀኝት ለ/ ታማኝነት ሐ/ ራስን መቆጣጠር መ/ ተጠያቂነት

37. ከሚከተሉት አንዱ የመልካም ባህሪ መላበስ ጠቀሜታ ነው፡፡

ሀ/ ክብርን፣ ታማኝነትን ለ/ መልካም ባህሪ አለመላበስን

ሐ/ ጠቃሚ ለውጦችን አለማምጣት መ/ በጓደኛ ዘንድ አለመከበር

38. በህይወት ስኬት ቁልፍ ሚና ይጫወታል

ሀ/ ለህግ ተገዥ መሆን ለ/ ዕሴቶችንና መርሆችን ማክበር

ሐ/ ህግና ደንብ ማክበር መ/ ራስን መቆጣጠር

39. እያንዳንዱ የት/ቤቱ አባል ምን ማድረግ እንዳለበትና ማድረግ እንደሌለበት መረጃ የሚሰጥ፡-

ሀ/ ለህግ ተገዥ መሆን ለ/ ራስን መቆጣጠር

ሐ/ የት/ቤት ህግና ደንብ ማክበር መ/ መርሆችን ማክበር

40. ከሚከተሉት የመልካም ባህሪ አለመላበስ ውጤት አይደለም፡፡

ሀ/ ያልተገባ አለባበስ ለ/ ስርቆት ሐ/ ታማኝ መሆን መ/ መዋሸት



LIVEWORKSHEETS